በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

## ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 1-10፤11-20/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 1/2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ** .......... - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024.......... - 2 -

ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......... - 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024.......... - 2 -

ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት .......... - 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ.......... - 2 -

የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር .......... - 2 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ.......... - 3 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ .......... - 3 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ .......... - 4 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 4 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024.......... - 4 -

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ.......... - 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር .......... - 5 -

ሁኔታ ትንበያ.......... - 5 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......... - 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......... - 6 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ.......... - 6 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.......... - 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ.......... - 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ.......... - 8 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጃንዋሪ ወር የመጨረሻዎቹ ቀናቶች አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ነገር ግን በጥቂት ቀናቶች የስምጥ ሸለቆና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ከነበረው የደመባ ሽፋን በመነሳት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፣ በጥቂት አካባቢዎችም ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በመካነ ሰላም51.4፣ በአማን 17.1፣ አምባማሪያም 11.4፣ በጋቲራ 17.4፣ በኮንሶ 23.6፣ በጂንካ 15.5 እና 13.8 በጭራ 45.2፣ በማጂ 35.5 እንዲሁም በተርጫ 36.8 በሚ.ሜ. ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የቀኑ ሙቀት መጠን ከ35-42 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል የመዠንግና የአኙዋክ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ የጅማና የሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም ከአማራ ክልል በጥቂት የምዕራብ ጎጃም ዞን ላይ ከ21-130 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-8 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከጋምቤላ የኑዌር ዞን፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ የምዕራብ ጉጂና ጥቂት የቦረና ዞኖች፣ ኢሉባቦርና ቡኖበደሌ ዞኖች፣ ከአማራ የደቡብና ሰሜን ወሎ እና የደቡብ ጎንደር ምስራቃዊው ክፍል፣ ከአፋር ዞን 4 እንዲሁም የደቡብ ትግራይ ላይ ከ6-20 ሚ.ሜ ከ4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ የጅማ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖበደሌ የምዕራብ ጉጂና ጥቂት የቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከአማራ የደቡብና ሰሜን ወሎ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን፣ የደቡብ ጎንደር ምስራቃዊው ክፍልና




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ሰሜን ሸዋ፣ ከአፋር ዞን 4፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ በጥቂት የመተከል ዞን እንዲሁም ደቡብ ትግራይ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናቶች የነበረው የአየር ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበረ። በሌላ በኩል በጥቂት ቀናት በአንዳንድ የመካከለኛው እና የደቡብ ስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ የበጋ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች በተጨማሪም በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የበጋን ወቅት እንደ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሚጠቀሙ የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና ስራ አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንፃሩም በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛውና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረው እርጥበት የበልግ እርሻን አስቀድሞ ለመጀመርና የማሳ ዝግጅት ለማከናወን የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 ድረስ
የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናቶች በታችኛውና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም በመካከለኛው ምስራቃዊ አባይ ላይ መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን በአንጻሩ በአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ፣ ተከዜ፣ ኦጋዴን ፣ አፋር ደናክል እና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ በፌብርዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያላው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በምዕራብ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱር ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ እና የሰሜን ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ እንዲሁም የዋግህምራ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ከጋምቤላ ክልል የመዠንግ እና ጥቂት የአኝዋክ ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛዉ ጎንደር እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ የባሌ፤ የምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፤ እንዲሁም የሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና ፋፈን ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣ ዞን እና 4 ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት እና የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት አልፎ አልፈ በሚኖሩት ቀናት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ፤ እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብእንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች (ካርታ 8) ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 11-20 Feb




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ11-20፣ 2024 የሚኖረው
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ የመጀመሪያው አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ። ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም በዚህ ወቅት የሚገኘው እርጥበት ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት እና የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ዘር ለመዝራት ጠቀሜታ የሚኖረው በመሆኑ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ይህንኑ እድል ለመጠቀም የሚያስችል ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛው እና የምስራቃዊ አባይ፣ የአዋሽ፣ በጥቂት የላይኛው ተከዜ እንዲሁም በአፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር ውሃ ሀብትን ለማሻሻል አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et